የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ

# የ2019 በጀት ዓመት ዓመታዊ የበጀት መግለጫ


አህመድ ሽዴ

የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር


ሰኔ 04/2018 ዓ.ም

BUDGET SPEECH

አዲስ አበባ • ADDIS ABABA

የ2019 በጀት መግለጫ (Budget Speech)

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት**

ዛሬ በመካከላችሁ የተገኘሁት በሚኒስትሮች ም/ቤት ተደግፎ ስለቀረበው የ2019 የፌዴራል መንግስት ረቂቅ በጀት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 77 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት ስለ በጀቱ መግለጫ ለማቅረብ ነው። ለረቂቅ በጀቱ መነሻ የሆኑትን አጠቃላይ ታሳቢዎችን እና የበጀቱን ዝርዝር መግለጫ ከማቅረቤ በፊት ባለፉት ዓመታት የኢትዮጵያን የማክሮ ኢኮኖሚ ጉዞ እና በመገባደድ ላይ ያለውን የበጀት ዓመት የኢኮኖሚ ዕይታ በአጭሩ አመልክቼ ተደግፎ የቀረበውን የ2019 የፌዴራል መንግስት በጀት ድልድል የተመሠረተባቸውን ታሳቢዎች እና ስለ በጀቱ ዝርዝር መግለጫ ለተከበረው ምክር ቤት አቀርባለሁ።

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት**

የኢኮኖሚ መረጃዎች በተጨባጭ እንደሚያመላክቱት፣ ባለፉት ዓመታት የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራምና የአስር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ በመደረጋቸው፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጣዊና ውጫዊ ጫናዎችን በብቃት በመቋቋም ጠንካራ አፈጻጸምና ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል። ከ2012-2016 ባሉት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ በየዓመቱ የ6.8 በመቶ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን፣ በ2017 ደግሞ የ9.2 በመቶ አስደናቂ እድገት ተመዝግቧል። በያዝነው በጀት ዓመትም ከመካከለኛው ምስራቅ ግጭት የመነጨ ጫናዎችን በመቋቋም፣ የ10.2 በመቶ ኢኮኖሚ ዕድገት እንደሚመዘገብ ተገምቷል። ይህም ኢትዮጵያን በአሁኑ ወቅት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እያስመዘገቡ ካሉ የዓለም ሀገራት መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚያሰልፋት ነው።

ይህንን ከፍተኛ እድገት በምናስመዘግብበት ወቅት ከቀድሞዎቹ ዓመታት ልዩ የሚያደርገው ለተከታታይ ዓመታት ፈተና ሆኖ የቆየውን የዋጋ ንረት በተቀናጀ የሪፎርም ሥራዎችና የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን በመተግበር እንዲሁም ምርታማነትን በማሳደግ በተጨባጭ መቆጣጠር መቻላችን ነው። በተለይም የተቀናጀ የገንዘብና የፊስካል ፖሊሲ እርምጃዎችን ተግባራዊ በማድረግ፣ ምርትና ምርታማነትን በማሻሻልና ጠንካራ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ እንዲሁም ቁርጠኛና ውጤታማ የኢኮኖሚ አስተዳደርን በማስፈን የዋጋ ግሽበትን በተሳካ ሁኔታ መቀነስ ተችሏል። እነዚህ እርምጃዎችም የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ዋጋ ግሽበት ወደ ነጠላ አሃዝ ደረጃ በማውረድ

አዎንታዊ ውጤት አስገኝተዋል። በተጨማሪም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በወሰድናቸው ጉልህ እርምጃዎችና በተለይ በግብርና ዘርፍ በሰብል ምርትና በእንስሳት ምርት፣ የምርቶች አቅርቦት ሰንሰለትን ውጤታማነት በማሳደግ እንዲሁም የከተማ ግብርናን በማበረታታት ረገድ ያስመዘገብናቸው ውጤቶች፣ የዋጋ መረጋጋትን ለማስፈንና ለዜጎቻችን ተጨባጭ እፎይታን ለመፍጠር ወሳኝ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

እንዲሁም ባለፉት ዓመታት ተግባራዊ በተደረጉት የገንዘብ ፖሊሲዎች ባንኮች የሚሰጡት አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ብድር የተገደበ ዕድገት እንዲኖረው መደረጉና የገንዘብ አቅርቦቱም ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን መደረጉ እና ባለፉት ሁለት ዓመታት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለበጀት ጉድለት መሸፈኛ የሚወሰድ ብድር ሙሉ ለሙሉ እንዲቆም መደረጉ የዋጋ ንረቱን ወደ ነጠላ አሃዝ ለማውረድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

በዚህም መሠረት፣ በነሐሴ 2014 ወደ 34.5 በመቶ አሻቅቦ የነበረው የአጠቃላይ የዋጋ ንረት በመጋቢት 2018 ወደ 9.4 በመቶ ነጠላ አሃዝ ዕድገት ማውረድ ተችሏል። በበጀት ዓመቱ የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት በየወሩ በሚያወጣው የሸማቾች ዋጋ ኢንዴክስ መሠረት፣ በምግብም ሆነ ምግብ ያልሆኑ ሸቀጦች ዋጋ ላይ የታየው ቅናሽ ይህንን አዎንታዊ ውጤት በግልጽ ያሳያል። ከዚህም በላይ የውጭ ምንዛሬ ለውጡ የዋጋ ንረትን እንዳያባብስ ቀድሞ የተቀናጀ ስራ በመሰራቱ የዋጋ ግሽበትን በከፍተኛ ደረጃ መቆጣጠር የተቻለበት ሆኗል። ይህም ይበለጥ የተረጋጋና የበለጸገ ኢኮኖሚ ለመገንባት የምንሄድበትን ጉዞ የሚያጠናክር ታላቅ ምዕራፍ ነው።

በተመሳሳይ፣ ባለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የገጠሙትን የውጭ ክፍያ ሚዛን ጫናና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ተግዳሮቶችን ከ2017 ጀምሮ ተግባራዊ እያደረግን ባለው የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም አማካኝነት በእጅጉ መቅረፍ የተቻለ ሲሆን ዘመናዊና ውጤታማ የውጭ ምንዛሬ አስተዳደር መዘርጋት ተችሏል፣ በተጨባጭና በዘላቂነት በኢኮኖሚ ውስጥ የነበሩ ማነቆዎችን ለመፍታት አስችሏል። በተለይም ወደ ገበያ መር የውጭ ምንዛሬ ስርዓት የተደረገው ሽግግር፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረትን በእጅጉ በመቅረፍ በህጋዊና በትይዩ ገበያ መካከል የነበረውን የውጭ ምንዛሬ ተመን ክፍተት በከፍተኛ ደረጃ ማጥበብ ተችሏል። ይህም የወጪ ንግድ ሚዛን ጉድለትን ለማጥበብ እና የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ችግርን ለመቅረፍ ትልቅ አስተዋጽኦ ከማድረጉም ባሻገር ለልማት አስፈላጊ የሆኑ ካፒታል እቃዎችን በተሻለ ሁኔታ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት እገዛ አድርጓል። በተለይ በ2017 በጀት ዓመት የሸቀጦች ኤክስፖርት ገቢ በ2016 ከነበረበት 3.8 ቢሊዮን ዶላር ወደ 8.3 ቢሊየን ዶላር በማደግ የ119% ጭማሪ አሳይቷል።

በያዝነው የበጀት ዓመትም በወጪ ንግዱ ይህንኑ ከፍተኛ አፈጻጸም ማስቀጠል በመቻሉ የንግድ ሚዛን ጉድለት በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። በተለይም የአገራችን ኩራት የሆነው የታላቁ የህዳሴ ግድብ በመጠናቀቁና ኃይል ማመንጨት መጀመሩ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከፍተኛ ዕገዛ ከማድረጉም በላይ ለጎረቤት ሀገራት የኤሌክትሪክ ኃይል ኤክስፖርት አቅርቦትን በማሳደጉ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ እንዲሆን አስችሏል።

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት**

በተመሰሳይ ማሻሻያው ትኩረት ካደረገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል የገንዘብ ፖሊሲያችንን ለማዘመን ተግባራዊ የተደረጉ ሥር ነቀል የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ተጠቃሽ ናቸው። የገንዘብ ፖሊሲ ማሻሻያው ዋና ዓላማ ዋጋን ለማረጋጋት፣ ተግባራዊ የተደረገውን የውጭ ምንዛሬ ማሻሻያ ውጤታማነት ለማሳደግ፣ እና የፋይናንስ ዘርፉን ጤናማነትና ዘላቂነት በማረጋገጥ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለመደገፍ ሲሆን ባለፉት ዓመታት የገንዘብ ፖሊሲ ማዕቀፉን ዘመናዊና በገበያ በሚወሰን የወለድ ምጣኔ እንዲመራ ለማድረግ ያስቻሉ የተለያዩ ማሻሻያዎች ተግባራዊ ተደርገዋል። ለአብነትም በኢኮኖሚው ውስጥ የአጭር ጊዜ የወለድ ምጣኔዎች አወሳሰንን ለማመላከትና በገበያ ወደ ሚመራ የወለድ ምጣኔ አወሳሰን የሚደረገውን ሽግግር ለመምራት እንዲያግዝ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የፖሊሲ ወለድ ምጣኔ ተግባራዊ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን፣ ይህም ለመጀመሪያ ጊዜ 15 በመቶ ሆኖ እንዲቀመጥ ተደርጓል። እንዲሁም፣ በሥራ ላይ ከነበሩት ቀጥተኛ ከሆኑ የገንዘብ ፖሊሲ መሳሪያዎች በተጨማሪ ቀጥተኛ ያልሆኑ የገንዘብ ፖሊሲ መሳሪያዎችም ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ ላይ እንዲውሉ የተደረገ ሲሆን፣ ለዚህም ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን ያካተተ የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥራውን እየመራ ይገኛል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ዝቅተኛ የባንኮች የተቀማጭ የወለድ ተመን ሙሉ በሙሉ ተነስቶ በገበያ እንዲወሰን እና የንግድ ባንኮች ከደንበኞቻቸው ጋር በገበያ ሁኔታዎች ላይ በመመሥረት የወለድ ተመኖችን በነፃነት እንዲደራደሩና እንዲወስኑ ሙሉ መብት ተ ሰጥቷል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይህንን የተዘረጋውን ዘመናዊ የገንዘብ ፖሊሲ የሚያጠናክሩ ሌሎች በርካታ ለውጦችን ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን፣ የፋይናንስ ዘርፉን ደህንነት ለማስጠበቅና ለማዘመን የተጀመሩ ስራዎችም ተጠናክረው ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ። በተለይም፣ የፋይናንስ ዘርፉን ለማዘመን የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ (Ethiopian Securities Exchange) መመስረት አንዱና ዋናው ነው። ይህ ዘመናዊ የካፒታል ገበያ ስርዓት ዝርጋታ በታቀደው መሠረት ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን፣ መንግሥትም ሆነ የግል ኩባንያዎች የረጅም ጊዜ የፋይናንስ ፍላጎቶችን ለማሰባሰብ የሚችሉበት ዘመናዊ መድረክ ሆኖ ለማገልገል ዕድል የሚከፍት በመሆኑ ለኢኮኖሚ ልማታችን እንደ ከፍተኛ ስኬት ሊታይ የሚገባው ነው። በአሁኑ ወቅት በዚህ ስርዓት ግብይቶች

እየተካሄዱ መሆናቸውን ስንመለከት የወደፊቱን በዚህ መስክ የሚገኘውን ከፍተኛ ውጤት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በገንዘብ ፖሊሲ ረገድ ተግባራዊ የተደረጉት እነዚህ ማሻሻያዎች ተግባራዊ በመሆናቸው ከፍተኛ ውጤት እየታየ ይገኛል። ለአብነትም በኢኮኖሚ ውስጥ የሚዘዋወረው ገንዘብ በዚህ ሥርዓት በአግባቡ በመገደቡ እና መንግስት የበጀት ጉድለቱን ለመሸፈን ከማዕከላዊ ባንክ በቀጥታ ይወስድ የነበረውን ቀጥታ ብድር ሙሉ በሙሉ ማቆም በመቻሉ የዋጋ ግሽበትን ከታሰበው በላይ በተሳካ ሁኔታ መቆጣጠር ተችሏል፣ እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ ስርዓት ማሻሻያ ትግበራው ውጤታማ እንዲሆን ከፍተኛ ዕገዛ አድርጓል።

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት**

ባለፉት ዓመታት መንግስት በኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ው ስ ጥ እጅግ ወሳኝ እና መጠነ ሰፊ ሊባል የሚችለውን የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ስራዎች ተግባራዊ በማድረጉ ስር የሰደዱ መዛባቶችን እና ለረጅም ጊዜ የዘለቁ መዋቅራዊ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ እየረዳ ይገኛል። ማ ሻ ሻ ያ ው በተለይም የኢኮኖሚ ፖሊሲን ውጤታማነት በማሻሻል፣ የግል ዘርፉን ሚና ለማጠናከር እና ሀገሪቱን ወደ ጠንካራ፣ ምርታማ እና አካታች እድገት ለመምራት በር የከፈተ ማሻሻያ ነው። የውጭ ምንዛሬ ተመን በገበያ የሚመራበት ሥርዓት በመዘርጋቱ ለንግድና ለአምራች ዘርፎች በውጭ ምንዛሬ አቅርቦትና ተደራሽነት ረገድ የተሻለ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር መርዳቱ ሊጠቀስ የሚገባው ስ ኬ ት ነው። እንዲሁም የገንዘብ ፖሊሲው እና የፋይናንስ ሥርዓቱ ዘመናዊ በመደረጉ የግሉ ዘርፍ በብድር አቅርቦት ረገድ የነበረበትን መዋቅራዊ ችግሮች በመቅረፍ የተሻለ የብድር አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ ተችሏል። በዚህም የግል ዘርፍ ኢንቨስትመንት ተስፋፍቷል፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰት ጨምሯል።

የ2019 በጀት መግለጫ (Budget Speech)

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት

እየተተገበረ የሚገኘው የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ፣ ሁሉንም ዘርፎች በትኩረትና በጥንቃቄ ያቀናጀ የተሟላ ስትራቴጂ ሲሆን፣ የፊስካል ፖሊሲ ማሻሻያ ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጣቸው መካከል አንዱና ዋነኛው ነው። በዚህ በፊስካል ፖሊሲ ማሻሻያ የተካተቱ ሪፎረሞች ከሌሎች አጠቃላይ የሪፎርም ሥራዎች ጋር ተቀናጅተውና ተጣጥመው እየተተገበሩ የሚገኙ ናቸው።

የፊስካል ፖሊሲ ማሻሻያው የሀገራችንን የፊስካል ቁመና ጤናማ ለማድረግና በጽኑ መሠረት ላይ እንዲገነባ ለማድረግ እና ዘመናዊ የታክስ ሥርዓትና አስተዳደርን ለማስፈን ያለመ ነው። ይህም የሀገር ውስጥ ገቢ ማሰባሰብ አቅማችንን በማጠናከር የምናልማቸውን ታላላቅ የልማት ፕሮጀክቶች በራሳችን አቅም ለመሸፈን፣ ለዘላቂ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ ኢንቨስትመንቶችን ለማስፋፋት እና ዘላቂ የፊስካል ሚዛንን ለማረጋገጥ እና የግሉን ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ ለማበረታታት በሚያግዝ ሁኔታ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። በተጨማሪም፣ በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ሂደት የሚያጋጥሙ ተጽዕኖዎችን ለመቋቋም፣ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የማኅበረሰብ ክፍሎች ለመደገፍ የሚያስችሉ እጅግ ወሳኝ የማህበራዊ ከለላ ድጋፎች ተቀርጸው በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል። የፊሲካል ፖሊሲ ማሻሻያዎች የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የሚጠይቀውን ጥብቅ የፊስካል ፖሊሲ (Fiscal Consolidation) መርህ መሠረት በማድረግ የተቀረጹ ከመሆናቸውም ባሻገር በአጠቃላይ በመንግስት ስርዓት ውስጥ የበጀት ቁጠባና ውጤታማነት ለማስፈን የሚያስችሉ ወሳኝ እርምጃዎችን ያካተተ ነው። በተጨማሪም የመንግስትን ብድር ዘላቂነትና ጤናማነት ለማረጋገጥ እና የመንግስት ልማት ድርጅቶችን አስተዳደር ዘመናዊና ውጤታማ በማድረግ የድርጅቶቹን ትርፋማነትና ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚኖራቸውን ድርሻ ለማሳደግ በርካታ ማሻሻያቸው ተግባራዊ ተደርገዋል።

ባለፉት ዓመታት የተጀመሩት እነዚህ ዘርፈ-ብዙ የፊስካል ፖሊሲ ሥራዎች ይበልጥ ተጠናክረው የቀጠሉ ሲሆን፣ ዋና ዋና ማሻሻያዎችና አፈጻጸሞችን እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

የታክስ ገቢን ከማሳደግ አንጻር አዳዲስ የታክስ ማሻሻያዎች ተግባራዊ ተደርገዋል። በዚህም የታክስ ስርዓቱን ዘመናዊ ለማድረግ፣ የታክስ መሠረትን ለማስፋት፣ አስተዳደራዊ ሂደቶችን ለማቃለል እና የግብር አሰባሰብን ለማሳለጥ የሚያስችሉ ሥራዎች ተግባራዊ ተደርገዋል። ለዚህም በተሟላ የማክሮ-ኢኮኖሚ ማሻሻያ የገቢ አሰባሰብን እና የታክስ አስተዳደር አገልግሎትን ለማሻሻል፣ እንዲሁም የታክስ ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሥራዎችን ያካተተው የብሔራዊ

መካከለኛ የመንግስት ገቢ ስትራቴጂ ተቀርጾ በአግባቡ ተግባራዊ በመደረጉ በ2017 በጀት ዓመት ሀገራዊ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ጋር ያለው ጥምርታ ከበርካታ ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1.6 መቶኛ (percentage points) በመጨመር በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 6.2 በመቶ በ2017 ወደ 7.7 በመቶ ከፍ ሊል ችሏል። በ2018 በጀት ዓመትም ይኸው አፈጻጸም ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን እስካሁን የታክስ አሰባሰቡ መረጃ እንደሚያመለክተው የሀገራዊ ታክስ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ አሁንም እንደሚጨመርና ወደ 9.5 በመቶ ከፍ እንደሚል ይጠበቃል። ለዚህም ውጤት የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የኤክሳይዝ ታክስ እና የገቢ ግብር አዋጅ ማሻሻያዎች፣ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ሥርዓት ማሻሻያ ተግባራዊ መደረጋቸው እና የግብር አስተዳደር ሥርዓቱም እየተጠናከረ መምጣት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ይታመናል፡፡ በተለይም ከኢንቨስትመንት ማበረታቻ ሥርዓት ማሻሻያው ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል በጥቅሉ ይተገበር የነበረውን አጠቃላይ የታክስ ነፃ መብት (Tax Holidays) አሠራር በመቀየር፣ ማበረታቻዎች ኢንቨስተሮች በሀገር ውስጥ ከሚያስመዘግቡት ተጨባጭ የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የካፒታል ፈጠራ (Performance-Based) ጋር በቀጥታ እንዲገናኝ የማድረግ ስልታዊ ሽግግር የተደረገ በመሆኑ በጥቅሉ ሲሰጡ የነበሩና ተገቢውን ወጤት የማያስገኙ ማበረታቻዎችን በመቀነስ ሀገሪቱ የምታጣውን ከፍተኛ ገቢ ለመቀነስ አስችሏል።

ከመንግስት ወጪ አንጻር፣ የመንግስት ወጪ የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ዝቅተኛ ገቢ ባለው የህብረተሰብ ክፍል ላይ የሚያስከትለውን የኢኮኖሚ ጫና ለማርገብ የሚያስችል የማህበራዊ ድጎማ ወጪ በጀት ተመድቦ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። ከዚህም ጋር በተያያዘ ለነዳጅና ለማዳበሪያ ድጎማ ከ2017 ጀምሮ ከፍተኛ በጀት በመመደብ ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን፣ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራምን ለማስፋፋት መንግስት ከፍተኛ በጀት በመመደብ ለበርካታ የከተማና የገጠር ተጠቃሚዎች ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም መንግስት የምግብ ዘይትንና መሠረታዊ መድኃኒቶችን በማቅረብ ረገድ የድጎማ በጀት በመመደብ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ዜጐች ድጋፍ አድርጓል። በሌላ በኩል ለፌዴራልና ለክልል የመንግስት ሠራተኞች ለተከታታይ ሁለት ዓመታት የደሞዝ ማሻሻያ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፣ ሠራተኞች በወቅቱ ከተከሰተው የዋጋ ንረት በተወሰነ ደረጃ ኑሯቸውን እንዲደጉሙ ማድረግ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ረገድ መንግስት ከፍተኛ ኃላፊነት የተሞላበት ውሳኔ በመውሰዱ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች በተደረጉ የማክሮኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ሊደርስባቸው ይችል ከነበረው የኑሮ ጫና ለመቋቋም የሚያስችል ድጋፍ አድርጓል።

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት

የመንግስት የፊስካል ጉድለት መጠን እየተሻሻለ ሲሆን በ2017 ዓ.ም በ7 አመታት ዝቅተኛ የሆነ የበጀት ጉድለት ተመዝግቧል። ይህም ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት አንጻር ሲታይ 1 በመቶ ብቻ ሲሆን፣ በ2014 ዓ.ም ከተመዘገበው 4.1 በመቶ አንጻር እጅግ ከፍተኛ መሻሻል ነው። በተጨማሪም የበጀት ጉድለትን ለመሸፈን የዋጋ ንረትን የማያባብሱ የፋይናንስ መሳሪያዎችን በመጠቀም በተለይም በመንግስት ግምጃ ቤት ሰነድ (T-Bills) እየተሸፈነ ይገኛል። ከብሔራዊ ባንክ የሚወሰደው ቀጥታ ብድር ሙሉ ለሙሉ ተቋርጦ የበጀት ጉድለትን በገበያ የፋይናንስ አማራጮች መሸፈን ከጀመርን እነሆ ሁለት ዓመታት ተቆጠሩ። ይህም በመሆኑ የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር ረገድ ከፍተኛ ትርጉም ያለው ዉጤት ተገኝቷል።

የመንግስትን የውጭ ብድር ጤናማ ከማድረግ አንጻር ከአበዳሪዎች ጋር በቡድን 20 (G-20) ሀገራት ውሳኔ የተሰጠውን የእዳ ሽግሽግ ዕድል በመጠቀም ከአበዳሪዎች ጋር በርካታ የዕዳ ሽግሽግ ድርድሮች ሲካሄዱ ቆይተዋል። በዚህ መሰረት በቡድን 20 የጋራ ማዕቀፍ ስር የኢትዮጵያን ዕዳ ሽግሽግ ለማፋጠን፣ ከሁለትዮሽ እና ከንግድ አበዳሪዎች ጋር በተቀናጀ መልኩ በመደራደር በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል። በመጋቢት 2017 ኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ኦፊሻል አበዳሪዎች ኮሚቴ (OCC) በዋና ዋና የፋይናንስ መለኪያዎች ላይ በተመሠረተ የመርህ ስምምነት (agreement in Principle(AIP)) ላይ የደረሱ ሲሆን፣ በመቀጠልም በሐምሌ 2017 የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሟል። ከአብዛኞቹ አበዳሪዎችም ጋር የመግባቢያ ሰነዱን መሠረት በማድረግ የሁለትዮሽ የዕዳ ሽግሽግ ስምምነቶች ተፈርመዋል። በተመሳሳይ ከግል አበዳሪዎች ጋር የዩሮ ቦንድ አበዳሪዎችን ጨምሮ የዕዳ ሽግሽግ ድርድሮች እየተካሄዱ የሚገኙ ሲሆን፣ ከአንዳንዶቹ ጋርም ስምምነት ለማድረግ ተቃርበናል። ይህ የዕዳ ሽግሽግ በየዓመቱ ለዕዳ ክፍያ የሚውለውን የውጭ ምንዛሬ ጫና በመቀነሱ ለልማት ፋይናንስ ተጨማሪ ሀብት ለማዋል አግዟል። እነዚህ የዕዳ ሽግሽግ ድርድሮች ሲጠናቀቁም የኢትዮጵያን የዕዳ ጫና ስጋት ወደ መካከለኛ ደረጃ ለማውረድ የሚያስችል ይሆናል።

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ትርፋማነትና ተወዳዳሪነት ለማሻሻል የሚከናወኑ ተግባራት ተጠናክረው ቀጥለዋል። የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ (EIH) ነባር የልማት ድርጅቶችን ለማዘመንና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ ከሚያከናውናቸው ስራዎች በተጨማሪ፣ ከግሉ ዘርፍ ባለሀብቶች ጋር በመቀናጀት በርካታ ግዙፍ የኢንቨስትመንት ዕድሎችንና ሜጋ ፕሮጀክቶችን በመሳብ

ላይ ይገኛል። ከእነዚህም መካከል በሀገራችን ታሪክ የመጀመሪያው የሆነው የማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት እና የቢሾፍቱ ኢንተርናሽናል ኤርፖርት ግንባታ ፕሮጀክት በዋነኛነት የሚጠቀሱ ሲሆን፣ ሌሎች ዘርፈ-ብዙ ስራዎችም የሀገሪቱን የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ራዕይ ዕውን ለማድረግ በከፍተኛ ሁኔታ እየተከናወኑ ይገኛሉ።

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት**

በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች እና የተገኙ ውጤቶች በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማዕከል ተደርጋ እንድትታይ የራሱ አዎንታዊ ሚና እየተጫወተ መሆኑን የሚያሳዩ መረጃዎች መኖራቸው ግልጽ ነው። በተለይም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት ለውጭ ባለሀብቶች ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ መዳረሻቸው እንድትሆን እየመረጧት ለመሆኑ የዓለም ኢኮኖሚ በችግር ላይ ባለበት ወቅት እንኳን የታየው የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰት ለዚህ ጉልህ ማስረጃ ነው። ከዚህም ባሻገር የቱሪስት ፍሰት መጨመርና ኢትዮጵያ የተለያዩ የዓለም ዓቀፍ ኮንፈረንሶችን ለማዘጋጀት ተመራጭ እየሆነች መምጣቷን ለመገንዘብ ተችሏል። ባለፉት ዓመታት ከተካሄዱ ኮንፈረንሶች በተጨማሪ ሀገራችን በቅርቡ COP በመባል የሚታወቀውን የ2027 የዓለም አቀፍ አየር ንብረት ለውጥ ጉባኤን COP32 ለማስተናገድ የተመረጠች ሲሆን፣ ለዚህም ሰፊ ዝግጅቶች እየተደረጉ ይገኛሉ። ይህም ሀገራችን በአየር ንብረት ጉዳዮች ላይ ያላትን ንቁ ተሳትፎ የሚያሳይ ሲሆን፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ እና ስትራቴጂያዊ ስኬት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ይህ ጉባኤ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲካሄድ መወሰኑ የሀገራችን፣ የአረንጓዴ አሻራ (Green Legacy Initiative) ስኬት እና የታዳሽ ኃይል ማስፋፋት ተግባር፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ማንኘታቸውን የሚያመለክት ነው። የCOP32ን ማስተናገዳችን ተጨማሪ የኢንቨስትመንት እድሎችን የሚስብ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ፋይናንስ ፍላጎቶቿን በዓለም መድረክ ላይ ለማቅረብ ከፍተኛ እድል ይፈጥርላታል።

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት**

በያዝነው በጀት ዓመት እየታየ ያለው የሀገራችን ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ካለፉት ዓመታት የተሻለ አፈጻጸም የታየበት ነው። ከኢኮኖሚ ዕድገት አንጻር በያዝነው በጀት ዓመት የ10.2 በመቶ ዕድገት

እንደሚመዘገብ መረጃዎች የሚያመላክቱ ሲሆን፣ የውጭ ዘርፍም ሆነ የፊስካል ዘርፉ አፈጻጸሞች ይህንኑ የሚያረጋግጡ ናቸው። ለአብነትም የፌዴራል መንግስት በጀት አፈጻጸምን ስንመለከት በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያዎቹ አስር ወራት ከብር 1 ትሪሊዮን በላይ የተጣራ የታክስ ገቢ የተሰበሰበ ሲሆን፣ ከባለፈው በጀት ዓመት በተመሳሳይ ጊዜ ከተሰበሰበው ጋር ሲነጻጸር የ72.2 በመቶ ዕድገት አለው። ይህም ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የተቀናጀ የታክስ ስርዓት ማሻሻያ ትግበራ ውጤታማነት ማሳያ ሲሆን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውም በተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን የሚያመላክት ነው። በሌላ በኩል የውጭ ኢኮኖሚ ዘርፉ በ2018 በጀት ዓመትም ከፍተኛ መነቃቃትን እያሳየ ይገኛል። በ2018 በጀት ዓመት የወጪ ንግድ በከፍተኛ ሁኔታ የተጠናከረ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ አስር ወራት ከወጪ ሸቀጦች ንግድ የተገኘው ገቢ 8.7 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን፣ ይህም በ2017 ተመሳሳይ ጊዜ ከተገኘው ገቢ አንጻር የ38.9 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፣ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከ10.5 ቢሊዮን ዶላር በላይ እንደሚደርስ ይጠበቃል። በተመሳሳይ በ2018 አስር ወራት ወደ ሀገር ውስጥ ለገቡ የገቢ ዕቃዎች የተደረገው ወጪ ወይም የኢምፖርት ዋጋ 18.4 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን፣ በ2017 ተመሳሳይ ጊዜ ከነበረው የኢምፖርት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር የ17.9 በመቶ ዕድገት አለው። ሆኖም በመካከለኛው ምስራቅ የተከሰተው ቀውስ በዚህ የውጭ ዘርፍ አፈጻጸም ላይ በተወሰነ ደረጃ ተጽእኖ ማሳደሩ የማይቀር ሲሆን፣ አፈጻጸሙ ከዚህ በላይ ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ መውሰድ ያስፈልጋል። የዋጋ ንረት በያዝነው በጀት ዓመት ከታህሳስ ወር ጀምሮ ወደ ነጠላ አሀዝ ዕድገት የወረደ ቢሆንም፣ በሚያዝያ ወር ላይ የተወሰነ ጭማሪ በማሳየት ወደ 11.7 በመቶ ከፍ ብሏል። ይህም የመካከለኛው ምስራቅ ቀውስ በፈጠረው የዓለም ሸቀጦች ዋጋ ማሻቀብ በተለይም ከነዳጅ ዋጋ ማሻቀብ ጋር ተያይዞ የተከሰተ ጭማሪ ሲሆን፣ የሚጠበቅ ነው። ሆኖም መንግስት ከዚህ ጋር በተያያዘ ከነዳጅ አቅርቦት አንጻር ይህ ከፍተኛ ተግዳሮት እንዳይሆን በወሰዳቸው እርምጃዎች የዋጋ ጭማሪው የከፋ እንዳይሆን ማድረግ ተችሏል። ሆኖም እርምጃው ከፍተኛ የፊስካል ጫና ማሳደሩንም ግንዛቤ መውሰድ ተገቢ ነው። በሌላ በኩል በማሻሻያው የተዘረጋው የውጭ ምንዛሬ ሥርዓት የውጭ ምንዛሬ ተመኑ የቀውሱ ተጽእኖ ሳይበግረው ጠንካራና የተረጋጋ ሆኖ መቀጠሉ ማሻሻያው በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ መሆኑን ያመላከተ ሲሆን፣ የውጭ ምንዛሬ ተመኑ የተረጋጋ ሆኖ መቀጠሉም የዋጋ ንረቱ ከዚህ የከፋ እንዳይሆን ማስቻሉን ማስታወስ ተገቢ ነው። በአጠቃላይ በያዝነው በጀት ዓመት የኢኮኖሚ አፈጻጸሙ በተያዘው ዕቅድ መሠረት ውጤት እያሳየ ሲሆን፣ ሁሉም የኢኮኖሚ አመልካቾች በመልካም አፈጻጸም ደረጃ ላይ መሆናቸውን የተደረገው ግምገማ ያሳያል።

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት**

ላለፉት ሁለት በጀት ዓመታት ሲተገበር የቆየው የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ አበረታች ውጤቶችን እያስገኘ በመሆኑ ጠንካራ የኢኮኖሚ መሰረት ለመጣል ለሚደረገው ጥረት ትልቅ አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል። በቀጣይም የማሻሻያ ስራዎቹን አጠናክሮ ተግባራዊ በማድረግ፣ በተለይም የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ለማሳደግ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር፣ በልዩ ልዩ ዘርፎች እየተመዘገበ ያለውን አበረታች ስኬቶች ይበልጥ በማጠናከር ሀገራችን የጀመረችውን የብልጽግና ጉዞ ከግብ እንደምናደርስ ጥርጥር የለውም። የ2019 የፌዴራል መንግስት ረቂቅ በጀትም መንግስት የያዛቸውን የማክሮ ኢኮኖሚ እቅዶች እንዲሁም አጠቃላይ የልማት እቅዱን ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ነው።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በ2019 በጀት ዓመት የ9.8 በመቶ ዕድገት እንደሚያሳይ ግምት የተወሰደ ሲሆን፣ የኢኮኖሚ ዕድገት ትንበያ በክፍላተ ኢኮኖሚ ሲታይ ግብርና የ7.1 በመቶ፣ ኢንዱስትሪ የ11.6 በመቶ እንዲሁም አገልግሎት የ8.5 በመቶ ዕድገት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። የመካከለኛው ምስራቅ ግጭት በዕድገቱ ላይ ተጽዕኖ እንደሚኖረው የተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች ያመላከቱ ሲሆን፣ የ2019 በጀትም ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ጦርነቱ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በተቻለ መጠን ለማርገብ በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ነው።

በሌላ በኩል በ2019 በጀት ዓመት አጠቃላይ የሸቀጦች ወጪ ንግድ ገቢ ጠንካራ ዕድገት እንደሚኖረው ተገምቷል። ለዚህም በዋናነት በገበያ ወደሚመራ የምንዛሬ ተመን የተደረገው ሽግግር ሕገ-ወጥ የውጭ ንግድ እንቅስቃሴዎችን በመቀነስ ወደ ሕጋዊ መስመሮች እንዲመለሱ በማድረጉ ነው። ይህም የውጭ ምንዛሬ ግኝቱን አስተማማኝ ከሆነ ምንጭ እንዲመነጭ እገዛ ከማድረጉም ባሻገር፣ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት በመሻሻሉ ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃዎችን ከውጭ ለማስገባት እንዲሁም በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ ስለሚያስችላቸው የኢንዲስትሪ ዕድገትን ለማፈጠን ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው ነው።

በተመሳሳይ የገቢ ዕቃዎች ዋጋ (value of goods import) በ2019 በጀት ዓመት 25.8 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ ነዳጅ ኢምፖርት ለማድረግ 6 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያስፈልግ ትንበያው ያመለክታል። ይህም በመካከለኛው ምስራቅ ጦርነት ምክንያት የአለም ገበያ ዋጋ ጭማሪን ተከትሎ የመጣ ነው። በሌላ በኩል የውጭ ምንዛሬ

መረጋጋትን የሚያጠናክሩ ማሻሻያዎች ተጠናክሮ የሚቀጥል በመሆኑ የብር የውጭ ምንዛሬ ምጣኔ የበለጠ የተረጋጋ እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል፡፡

የሸቀጦች ዋጋ ዕድገት በመገበደድ ላይ በሚገኘው በ2018 በጀት ዓመት በተከታታይ ቅናሽ በማሳየት ለመጀመሪያ ጊዜ ከታህሳስ ወር 2018 ጀምሮ ወደ አንድ አሃዝ ወርዶ የነበረ ቢሆንም በመካከለኛው ምስራቅ የተቀሰቀሰውን ጦርነት ተከትሎ የተወሰነ የመጨመር አዝማሚያ በማሳየት በሚያዝያ ወር 2018 ላይ ወደ 11.7 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡ በሌላ በኩል መንግሥት የመካከለኛው ምስራቅ ጦርነት ያስተከተለውን ጫና ለመቀነስ በከፍተኛ ዋጋ ከውጭ የሚገዛውን ነዳጅ ድጎማ በማድረግ ለህብረተሰቡ እያቀረበ ሲሆን፣ ሌሎች ተጓዳኝ የፖሊሲ እርምጃዎችን ተግባራዊ በማድረግ የዋጋ ንረቱን ይበልጥ ለመቆጣጠር ይሰራል፡፡ የባንኮች የገንዘብ አቅርቦትና የብድር መጠን በቀጣዩ የበጀት ዓመት ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት ጋር የተጣጣመ ዕድገት እንደሚኖራቸውና ለዋጋ ዕድገት መረጋጋትም እንደሚያግዙ ትንበያው ያሳያል፡፡

በፊስካል ፖሊሲ ረገድ የመንግስትን እምቅ የገቢ አቅም አሟጦ ለመጠቀም አዳዲስና በሥራ ላይ ያሉ የታክስ ፖሊሲ ማሻሻያዎች ተጠናክረው ይተገበራሉ፡፡ በዚህም የታክስ ማበረታቻን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ማሻሻያ በተለይም የገቢ ግብር እፎይታን በማስቀረት በቅናሽ መጣኔ እንዲሁም ነጻ የጉምሩክ ቀረጥ መጣኔዎችን በማስቀረት በዝቅተኛ የጉምሩክ ቀረጥ መጣኔ የመተካት አሰራር እየተዘረጋ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የኤክሳይዝ ስታምፕ አስተዳደር ሥርዓት በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረቶች እየተደረጉ ሲሆን፣ የታክስ ዲጂታይዜሽንን ጨምሮ የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች ተግባራዊ በማድረግ ተጨማሪ ገቢ ለማሰባሰብ እንደሚቻል ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ከልማት አጋሮች ጋር ያለውን ስትራቴጂካዊ ትብብር በማጠናከር የውጭ ሀብት አሰባሰብን ለማሻሻል የሚሰራ ሲሆን፣ ከልማት አጋሮች በበጀት ድጋፍ መልክ የሚገኙ የውጭ ሀብቶች ለበጀት መሸፈኛ በገቢ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

የ2019 የፌዴራል መንግስት ረቂቅ በጀት ሲዘጋጅ፣ የመንግስት ወጪ ፖሊሲ የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን ከማስቀጠል ባሻገር ከዋጋ ዕድገት ጋር ተያይዞ ዝቅተኛ ገቢ ባለው የህብረተሰብ ክፍል ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ ለማርገብ ለሚያስችሉ የማህበራዊ ወጪዎች በቀጣይም ትኩረት የሚደረግበት ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የመንግስት ወጪ ፖሊሲ በጥብቅ ፊስካል ዲሲፕሊን እንዲመራ የሚደረግ ሲሆን፣ የመንግስት ሀብት ቅድሚያ ትኩረት ለሚሰጣቸው ወጪዎች እንዲመደብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ከመደበኛ ወጪዎች ውስጥ ለግዴታ ወጪዎች ማለትም ለደሞወዝ፣ ለዕዳ ክፍያ እና ለሌሎች የግዴታ ወጪዎች የሚያስፈለገው በጀት ከተደለደለ በኋላ፣ ቀሪውን

የቅድሚያ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ጉዳዮች ለመደልደል ተሞክሯል። በተጨማሪም የሥራ ማስኬጃ መደበኛ ወጪ በቁጠባ ላይ የተመሠረተ አጠቃቀም እንደሚኖር ከግምት ተወስዷል። የዕዳ ክፍያን በተመለከተ የተወሰኑ የልማት ድርጅቶች ማለትም የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽ እና የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ ብድር የመክፈል አቅም ውስን በመሆኑ የውጭ ዕዳ ክፍያዎቻቸው በበጀት ውስጥ እንዲካተት የተደረገ ሲሆን፣ ለማዳበሪያ ድጎማ የሚውል በጀት ብር 100 ቢሊዮን እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል። እንዲሁም ለነዳጅ ድጎማ ብር 20 ቢሊዮን ብር ታሳቢ የተደረገ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ካፒታልን ለማሳደግ 116.4 ቢሊዮን ብር ከመንግስት ግምጃ ቤት የተመደበ ነው። በተጨማሪም ለልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ማስፋፊያ የሚያስፈልገው የወጪ በጀት ከግምት ውስጥ የገባ ሲሆን፣ የካፒታል ፕሮጀክቶች ወጪ በጀት በዋናነት የነባር ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን ወጪ እንዲያካትት ተደርጓል።

ከትሬዠሪ የሚመደበው የክልሎች የበጀት ድጋፍ በ2018 የተደረገውን የክልል ሠራተኞችና ተሿሚዎች የደሞዝ ጭማሪ ማስተካከያ ዓመታዊ ወጪን በ2018 ከጸደቀው የክልሎች የጥቅል በጀት ድጋፍ በጀት ጋር በመደመር ለ2019 በጀት ዓመት የ5 በመቶ ጭማሪ እንዲኖረው ተደርጓል።

በአጠቃላይ የ2019 የመንግስት ወጪ ፖሊሲ የፊስካል ቁመናን ለማጠናከር እና የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባትን በማያስከትል መልኩ የተዘጋጀ ነው። ከዚህ አንጻር የ2019 የፌዴራል መንግስት ረቂቅ በጀት የተመጠነ የበጀት ጉድለት እንዲኖረው ተደርጎ የተዘጋጀ ነው።

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት**

ከላይ የተጠቀሱትን የማክሮ ኢኮኖሚ እና የፊስካል ፖሊሲ ታሳቢዎችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀውን እና ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር ሰፊ ውይይቶች ተደርጎበት በሚኒስትሮች ም/ቤት ተደግፎ የቀረበውን የ2019 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ረቂቅ በጀት እንደሚከተለው በዝርዝር አቀርባለሁ።

በገቢ ረገድ በ2019 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ጠቅላላ ገቢ የውጭ ዕርዳታን ጨምሮ ብር 1.8 ትሪሊዮን እንደሚሆን ተገምቷል። ይህም በ2018 በጀት ዓመት ይሰበሰባል ተብሎ ከተገመተው ጠቅላላ ገቢ አንጻር የ17.4 በመቶ ዕድገት ያለው ነው። ከዚህ ውስጥ ብር 1.5 ትሪሊዮን ወይም 82 በመቶው ከታክስ ገቢ፣ ብር 120.4 ቢሊዮን ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች፣ ብር 83.4 ቢሊዮን ከልማት

አጋሮች የቀጥታ በጀት ድጋፍ እንዲሁም ብር 121.6 ቢሊዮን ከፕሮጀክቶች ዕርዳታ እንደሚሰበሰብ ታሳቢ ተደርጓል። በአጠቃላይ በ2019 በጀት ዓመት ከሀገር ውስጥ ምንጮች ማለትም ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች እንደሚሰበሰብ የታቀደው ገቢ ብር 1.6 ትሪሊዮን ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ ገቢው 88.7 በመቶውን ይሸፍናል። ቀሪው 11.3 በመቶ ደግሞ ከውጭ ዕርዳታ እንደሚገኝ የታቀደ ነው። ከታክስ ምንጭ የተያዘውን የገቢ ዕቅድ ለማሳካት ከላይ እንደገለጽኩት በታክስ ፖሊሲ እና በታክስ አስተዳደር ረገድ የተያዙትን ማሻሻያዎች በተቀናጀና በተጠናከረ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጓል። ከውጭ ዕርዳታ የሚገኘው ገቢ በበጀት ድጋፍ መልክ የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ለመደገፍ ከልማት አጋሮች የሚሰጠውን ድጋፍ ያካትታል።

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት**

የፌዴራል መንግሥት የ2019 በጀት ዓመት የወጪ በጀት ድልድል ከላይ የገለጽኩትን የወጪ የትኩረት አቅጣጫዎች መሰረት በማድረግ የተደለደለ ነው። በዚህም መሰረት አጠቃላይ የፌዴራል መንግስት የ2019 ጠቅላላ ወጪ በጀት ብር 2.3 ትሪሊዮን ሲሆን፣ ይህም በ2018 በጀት ዓመት ከፀደቀው የወጪ በጀት አንጻር የብር 411.5 ቢሊዮን ጭማሪ ወይም የ21.3 በመቶ ዕድገት አለው። ከዚህ የወጪ በጀት ውስጥ ብር 1.2 ትሪሊዮን ለመደበኛ ወጪ፣ ብር 568.2 ቢሊዮን ለካፒታል ወጪ፣ ብር 520.6 ቢሊዮን ለብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የበጀት ድጋፍ እና ብር 14 ቢሊዮን ለክልሎች ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ የተመደበ በጀት ነው።

ከላይ ከቀረበው ጠቅላላ የፌዴራል መንግስት የወጪ በጀት ውስጥ 52.9 በመቶ የሚሆነው (ከፍተኛው ድርሻ) ለመደበኛ በጀት የተመደበ ነው። ይህም በያዝነው 2018 በጀት ዓመት ለመደበኛ በጀት ከተመደበው አንጻር የ16.5 በመቶ ዕድገት አለው። ከዚህ ጠቅላላ የመደበኛ ወጪ ውስጥ ብር 542.1 ቢሊዮን ወይም 43.8 በመቶ የሚሆነው (ከፍተኛው ድርሻ) የተደለደለው ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ዕዳ ክፍያ ሲሆን፣ ብር 236.4 ቢሊዮን ወይም 19.1 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ለማዳበሪያና ለነዳጅ ድጎማ እንዲሁም የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅትን ካፒታል ለማሳደግ የተመደበ በጀት ነው። ለመንግስት ባለ በጀት መ/ቤቶች ለደሞዝ፣ ለአበልና ለልዩ ልዩ ክፍያዎች የተመደበው ጠቅላላ በጀት ብር 170.8 ቢሊዮን ወይም 13.8 በመቶ ሲሆን፣ ይህም በ2018 በጀት ዓመት ከተያዘው ተመሳሳይ ወጪ አንጻር የ22.6% ጭማሪ አለው።

በሌላ በኩል ለ2019 በጀት ዓመት ለፌዴራል መንግሥት ለካፒታል በጀት የተደለደለው ብር 568.3 ቢሊዮን ከጠቅላላ የወጪ በጀቱ የ24.3 በመቶ ድርሻ ሲኖረው፣ ለ2018 በጀት ዓመት ከተመደበው አንጻር የብር 153 ቢሊዮን ጭማሪ ወይም የ36.8 በመቶ ዕድገት አለው። የካፒታል በጀት ወጪ አሸፋፈኑ ሲታይ ብር 424.8 ቢሊዮን ከትሬዠሪና ከመ/ቤቶች የውስጥ ገቢ፣ ብር 112.6 ቢሊዮን ከፕሮጀክቶች ዕርዳታ እና ብር 30.9 ቢሊዮን ከፕሮጀክቶች ብድር ለመሸፈን የተያዘ ነው። ለ2019 ከተመደበው ጠቅላላ የካፒታል በጀት ውስጥ ከፍተኛ በጀት የተመደበላቸው የሥራ ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው።

- ለአገናኝ መንገዶች ግንባታ እና ነባሮቹን ለማጠናከርና ለማሻሻል ለተጀመሩ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 109 ቢሊዮን እንዲሁም ከውጭ ዕርዳታ እና ብድር 12.8 ቢሊዮን ብር በጠቅላላ 121.8 ቢሊዮን በጀት ተደግፎ የቀረበ ነው።

- ለከፍተኛ ትምህርት ነባር ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ፣ ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት እና ለአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፖኬጅ ከትሬዠሪና ከውጭ ፕሮጀክቶች ብድርና ዕርዳታን ጨምሮ በጠቅላላው ብር 61.3 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል።

- የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት ለነባርና ለትላልቅን አነስተኛ መስኖዎች ግንባታ እንዲሁም በቆላማ አካባቢዎች ምርምርና የቴክኖሎጂ ስርፀት በማድረግ የአካባቢውን ህብረተሰብ ኑሮ ለማሻሻል የውጭ ፋይናንስን ጨምሮ ብር 30.5 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል።

- ለመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ብር 14.3 ቢሊዮን ተደግፎ የቀረበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 4.3 ቢሊዮኑ ከመንግስት ግምጃ ቤት ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን ለሟሟላት የተደገፈ ነው።

- በገጠር የስራ ዕድልና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከመንግስት ግምጃ ቤትና ከውጭ ሀብት ብር 48.7 ቢሊዮን ለገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የተመደበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 45.1 ቢሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤት ተደግፎ የቀረበ ነው። በተመሳሳይ ለከተማ ምግብ ዋስትናና ልማታዊ ሴፍቲኔት ብር 24.1 ቢሊዮን የተመደበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 15 ቢሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤት ተደግፎ የቀረበ ነው። በአጠቃላይ ለተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ለምግብ ዋስትና እና ለከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት የልማት አጋሮችን ሳይጨምር ከመንግስት ግምጃ ቤት ብቻ ብር 60 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል።

- በግብርናው ዘርፍ ለተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ 5.1 ቢሊዮን የተደገፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 109.0 ሚሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤት የተመደበ ነው።
- እንዲሁም ለጤና ዘርፍ ጠቅላላ ብር 91.8 ቢሊዮን ተደግፎ የቀረበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 46.2 ቢሊዮኑ ከመንግስት ግምጃ ቤት የተመደበ ነው።

በሌላ በኩል ለ2019 በጀት ዓመት ለክልል መንግሥታት ተደግፎ የቀረበው ጠቅላላ የበጀት ድጋፍ ብር 520.6 ቢሊዮን ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 511.7 ቢሊዮን የሚሆነው የሚሸፈነው ከመንግስት ግምጃ ቤት ነው። ቀሪው ብር 8.9 ቢሊዮን ደግሞ ከፕሮጀክት ዕርዳታ የሚሸፈን ይሆናል። በሌላ በኩል የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማስፈጸም ለክልሎች ለ2019 በጀት ዓመት ብር 14 ቢሊዮን የበጀት ድጋፍ ተደልድሏል። ይህም የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንን ለማረጋገጥ የሚያግዙ የአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ለስራ ዕድል ፈጠራ እና በክልሎች ለሚካሄዱ ለአነስተኛ እና መካከለኛ መስኖ ልማት ካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውል ነው።

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት**

ከዚህ በላይ በዝርዝር ለማቅረብ እንደሞከርኩት በ2019 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ከሀገር ውስጥ የገቢ ምንጮች እንዲሁም ከውጭ ዕርዳታ በድምሩ ብር 1.8 ትሪሊዮን ገቢ እንደሚሰበሰብ በዕቅድ ተይዟል። እንዲሁም ለመደበኛ፣ ለካፒታል እና ለብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የበጀት ድጋፍና የዘላቂ የልማት ግቦች ማጠናከሪያ ወጪን ጨምሮ ጠቅላላ ብር 2.3 ትሪሊዮን በጀት ተደግፎ ቀርቧል። በዚህም መሠረት የቀጣዩ የ2019 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት የተጣራ የበጀት ጉድለት ብር 308.6 ቢሊዮን ሲሆን፣ ይህንንም የበጀት ጉድለት ብር 5.7 ቢሊዮን ከውጭ እና ብር 302.9 ቢሊዮን ከሀገር ውስጥ የተጣራ ብድር በመውሰድ እንዲሸፈን የታቀደ ነው። ይህ የተጣራ የበጀት ጉድለት ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ደግሞ 1.4 በመቶ ነው። ለ2019 በጀት ዓመት የተቀመጠው ይህ አጠቃላይ የተጣራ የበጀት ጉድለትም መንግስት በተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የተረጋጋ ኢኮኖሚ ለማስፈን ካስቀመጠው ግብ ጋር የተጣጣመ ነው። የሀገር ውስጥ ብድር አወሳሰዱም የመንግስት ግምጃ ቤት ሰነዶችን በመሸጥ ከገበያው ለማግኘት የታቀደ ሲሆን የውጭ ብድሩ ከልማት አጋሮች በበጀት ድጋፍ መልክ እና ለፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በሚወሰድ ብድር ለመሸፈን የታቀደ ነው። ከሀገር ውስጥ የሚወሰደው ብር 302.9 ቢሊዮን የተጣራ ብድር ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 1.3 በመቶ ነው።

**የ2019 በጀት መግለጫ (Budget Speech)**

ለ2019 ተደግፎ የቀረበው ይህ ረቂቅ የፌዴራል መንግስት በጀት በያዝነው በጀት ዓመት ተግባራዊ ከተደረገው በጀት ጋር ሲነጻጸር ጭማሪ ቢኖረውም ይህ ጭማሪ በአብዛኛው ከመካከለኛዉ ምሥራቅ ቀዉስ ጋር የተያያዙ ወጪዎች ታሳቢ ያደረገ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው። ይህ በጀት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ እና የዉጭ ኢኮኖሚያዊ ቀዉሶችን ተከትሎ የሚመጣዉን ጫና ለመቋቋም ያለመ ነው። በመሆኑም ባለበጀት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት ለታለመለት ዓላማ በቁጠባና በላቀ ውጤታማነት ጥቅም ላይ ማዋል እንዳለባቸው ከፍተኛ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል። በተጨማሪም የሚፀድቀውን በጀት የመንግስትን የፋይናንስ፣ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ህጎችን እና ሥርዓቶችን ተከትለው ስራ ላይ በማዋል የወጪ ቁጠባ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህንንም ለማረጋገጥ የክትትልና የቁጥጥር ስራውን በማጠናከር ከሥርዓቱ ውጭ ለሚደረግ የበጀት አጠቃቀም ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ሥራ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

በአጠቃላይ፣ የበጀት ጥያቄያቸውን በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳና በፕሮግራም በጀት ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ላቀረቡ አስፈጻሚ አካላት፣ እንዲሁም ረቂቅ በጀቱ ለምክር ቤቱ እንዲቀርብ በማድረግ ገንቢ ውይይት ላካሄደው የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት የበጀት መረጃዎችን ለሕዝብ በማስተላለፍ ላበረከቱት አስተዋጽኦ በመ/ቤቴ ስም ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ።

በመጨረሻም፣ ይህ የ2019 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት በጀት በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን እየተመኘሁ ከዚህ ጋር ተያይዞ የቀረበውን የ2019 ፕሮግራም በጀት የተከበረው ምክር ቤት እንዲያጸድቀው በአክብሮት እጠይቃለሁ።

**አመሰግናለሁ።**